የምርት ግብዓት መጠን የተጠቃሚውን ሂሳብ እንዲወራረድ ያደርጋል፤ የተወራረደ ስለመሆኑ ሚኒስቴሩ እንዲያውቀው ይደረጋል።

## 28. የጉምሩክ ቁጥጥር

1) ወደ ፋብሪካው የሚገቡ የምርት ግብዓቶችንና ተመርተው የሚወጡ ምርቶች ለፋብሪካው በሚመደብ የጉምሩክ ኦፊሰር ቁጥጥር ይደረጋል፣
2) በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ድንገተኛ ቁጥጥር ይደረጋል፣
3) በአንቀጽ 26 ስለማወራረድ በተገለጸው ሁኔታ በስርዓቱ የገቡ የምርት ግብዓቶች ለታለመላቸው አላማ ስለመዋላቸወ ቁጥጥር ይደረጋል።

## 29. የቦንድድ ፋብሪካ ፈቃድ ስለሚታደስበት ሁኔታ

1) ከሚኒስትሩ የታደሰ ሰርተፍኬት እና የግብዓት ምርት ጥመርታ በማያያዝ ተጠቃው ማመልከቻ ያቀርባል፣
2) የቅ/ጽ/ቤቱ አስፈላጊውን ማጣራት በማድርግ ፈቃዱ እንዲታደስ ያደርጋል፣ ስለመታደሱ የሚመለከታቸው እንዲያውቁት ያደርጋል።

# ንዑስ ክፍል አራት

## የተጠቃሚው ፣ ቅ/ጽ/ቤቶችና የኦፊሰር ተግባር ኃላፊነትና ግዴታ

## 30. የተጠቃሚው ግዴታና ኃላፊነት

1) ማንኛውም የስርዓቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሚይዘው መዝገብ ባለስልጣኑ ቁጥጥሩን በአግባቡ ለማከናወን በሚያመች መልኩ ማደራጀት ይኖርበታል፣
2) ለአገልግሎት አሰጣጥና ለቁጥጥር አመቺ የሆነ በአውቶሜሽን የተደገፈ ስርዓት ያለው መሆን አለበት፣፣
3) የኮምፒውተር ስርዓቱን በተመለከተ መረጃውን ማደራጀት ያለበት ፍቃዱ በተሰጠው በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ነው፣
4) በፋብሪካ ይዘት ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም ለውጦች በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ እና ውሳኔ ማግኘት አለበት፣የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤትም በ5 የስራ ቀናት ውሳኔ መስጠት አለበት፣
5) የመጋዘን ፈቃዱን ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ ማስተላለፍ አይቻልም፣
6) በህግ በተወሰነው ጊዜ የማወራረድ እና፣
   ሀ/ ለምርት የሚገቡ የምርት ግብዓቶችን እና የቀረጥ መጠኑን፤
   ለ/ በመጋዘኑ የሚገኙ ዕቃዎችን የሚያመለክቱ፤
   ሐ/ ያለቀለትን ምርት ዓይነትና መጠን፤
   መ/ ወደ ውጭ የተላከውን ምርት፤

